# እጅግ አጣዳፊ የተቀደሰ ፍልሚያ
## ማስተካከያና ማብራሪያ

ሚያዝያ ፯ / ፪ ሺህ

ለክ. አቶ. መለስ ዜናዊ ጠ. ሚኒስትር
ለክቡራን የታላቁ የኢ.ት. ሕዝብ የጉዳዩ ባለሞያ ልጆች በያላችሁበት
ከኮማንደር አሰፋ ሰይፉ ኢትዮጵያዊ ስደተኛ

## ያንድ ወገን ሕይወት ሳይጠፋ- አንድ ከብት ሳይበክት - ጠብታ ውሃ ሳይባክን ወገንን ከዕልቂት ማዳን ከመመጽወትም መገላገል

በዚች ጽሑፍ ማስተካከያን፥ ማብራሪያንና መገናኝያ ብዙሃንን እዳስሳለሁ

## ፩- ማስተካከያ

ሀ_ ይህን ፍልሚያ መጋቢት ፬ ቀን ከላክሁ በኋላ ፍልሚያዉን
በተመለከተ በቀጥታና በተዘዋዋሪ መልክ ያገኘኋቸዉን ሳስቀድም
_ ጠ. ሚኒስትሩ መንፈቃዊ የሥራ መግለጫቸዉን ለም.ቤት
ባቀረቡበት ዕለት በቦረናና/ ሲዳማ ከብት በጎርፍ ሞተ የተባለዉን
አስተባብለው “ሊሸጧቸውም ይችላሉ” ያሉት
_ የኦሮሞ ክልል ዋና አስተዳዳሪም በክልላቸው ዉስጥ በጎርፍም ሆነ
በድርቅ የሞተ ሰዉም እንስሳም የለም ሲሉ በተናገሩበት ወቅት
ይናገሩት ከነበረው ጭብጥ ጋር ግኑኝነት አለው የሚያስብል
ነገር ለተቀደሰው ተፋላሚ ስላልነበረ
_ እንደዚሁም የጠ. ሚኒስትሩ በአዋሽ መጨረሻ ተንዳሆ - ዱብቲ
አካባቢ መሠራት ላይ ያለዉን ግድብ ሲጎበኙ ማሣየት
_ ዋልታ ላይ መጋቢት 26 ቀን
“የድርቅ አደጋዎችን ለዘላቂነት ለመከላከል በሚያስችሉ መፍትሂዎች ዙሪያ
ትኩረት መስጠት እንደሚገባ ተገለፀ “
የሚሉት ኹሉ ለኣጣዳፊው የተቀደሰ ፍልሚያ የጅ አዙር መልስ
ይመስላል። የቀጥታው መንገድ ምን አጠፋ? በአለኹበት የስደት አገር

ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ስፅፍ መልስ ያላገኘኹት አንድ ጊዜ ብቻ ነው። እሱዉም በኹለተኛው ቀን ፕሮፌስር አሥራት ( መሬት ይቅለለዉና) ለሕክምና ለመውጣት እንደተፈቀደለት በአምባሳደራቸው አማካይነት ከአዲስ አበባ መግለጫ በመስጠት አዎንታዊ መልሳቸእዉን በሰጡበት ጊዜ ነው ( ይህን ስል በኔ ደብዳቤ ብቻ ወጣ ለማለት ሳይሆን የመጨረሻዋ ገለባ የግመልን ወገብ ሠበረች እንደሚሉት ይሆን ይሆናል ለማለት መሆኑን ወገን እንዲረዳልኝ አበክሬ አሳስባለሁ)

ታድያ አገረንና ወገንን የሚገዙት ጠቅላይ ሚኒስትር፦ ለሚገዙት ሕዝብ ደኅንነትና እንስሳቱም በክተው ሳይቀሩ ለጥቅም እንዲውሉ ውኃውም እንዳይባክን ለቀረበው የተቀደሰ አሳብ (በግርድፉም ቢሆን) የሚሰጡት መልስ ይህ ከሆነ ሥልጣን ከያዙ ጀምሮ እርሳቸውና ግብረ-ዐበሮቻቸው የሚታሙበትን ማጠናከር አይሆንባቸውም ወይ?

ከዚህ በላይ ያሉት ከተቀደሰው ፍልምያ ጋር ምን ያህል ተቀራራቢነት እንዳለው ወገን ይፍረድ። ለተፋላሚው ግን ሰማይና ምድር ነው። ይህን ስል የተሠራው፤- እንደ አዋሽ ግድብ ዓይነቱ ጥቅም ቀላል እንዳልሆነ በማመን አዋሽ እዚያ እስቲደርስ እንኳን ጥቅሙ ሳይሆን ጉዳቱም እንዳለ ምናልባትም እንደሚባባስ ሳልገነዘብ ብቀር በደል ይሆናል ብዬ አምናለሁ.

## ፱- ማብራሪያ

በወገን በኩል ደግሞ በነቀፋ፦ በአስተያየት ወዘተ መልክ የደረሱኝን ጠቃቅሼ ላብራራ

- ወያኔን አታውቅም? ለራሱ መነገጃ አዲስ ዘዴ ሰጠኸው። ነጻ ቦርድ ያልኸውን ይቀበላል ብለኽ ካስብኽ መመርመር ያስፈልግሃል
- ወያኔ ሕዝቡ በተለያየ መልክ እንዲያልቅ/እንዲቀነስ በዕቅድ መሥራቱን አጥተኸው ነው? መለስ ራሱ ኢትዮጵያ ሃያ ሚሊዮን ሕዝብ ይበቃታል ያለውን አልሰማሁም ልትል ነው?
- ኀያላኑ የዓለም ሕዝብ በድርቅ፦በበሽታ፦ በጦርነት እንዲቀነስ ዐቅዶ መሥራቱን አታውቅም? ወይስ መለስ የነሱ መሣርያ መሆኑን አላውቅም ለማለት ነው?
- ሥልጣን ያለው ባንድ መዳፍ ላይ ከሚቆጠሩት ጣቶች ባልበለጡ የሕወሀት ግምባር ቁልፍ መሪዎች የተያዘ መሆኑን ሳታውቅ ቀርትህ ነው? መለስ በእነዚህ ሰዎች ቁጥጥር ሥር መሆኑ ሲሰለቸው በቃኝ! ለቀቅ ስያደርጉት ደግሞ የመቆየት አዝማምያ ማሣየቱንስ አልተገነዘብህም ማለት ነው?

ሰከን ሲል ደግሞ

- ውጪ ያለው ኑሮውን አናግቶ ቢገባ ተመልሶ መግቢያው የት ሊሆን ነው?
- እዚያስ የመኖሪያው ሆናቴ እንዴት ይሆናል?
- እንዳሠብከው ምክሩ ( ቦርዱ) ሙሉ ነጻነት አግኝቶ ሊሠራ ይችላል የሚል ዕምነት አለህ ወይ?

_ ውጪ ያለው ባለሞያ መለስን ዐምኖ የሚገባ ይመስልሃል ወይ?  ወዘተ

እንግዲህ እነዚህና መሰል ጥያቄዎች መልስ ሊያገኙ የሚችሉት ከጠቅላይ ሚኒስትሩ መልስ በኋላ ይህናል፡፡ የአደጋው አይቀሬነትን አስቸኳይነት መልሱን እንደሚያፋጥን ተስፋ አለኝ

እስካሁን ለተ.መ.ማ. ዋና ጸሓፊ ከ $500 ሚሊዮናቸው በዕቅድ ለተደገፈ መፍትሂ ድርሻችንን እንዲያስቡልን ከመጻፍ ሌላ የታገድሁት ለማዋጣት እንዳይመስልብኝ ብዬ ነው;፡

## ፫ መገናኚያ ብዙሃን

በአጠቃላይ በአገር ጉዳይ በተልይ ግን የአፋጣኙን የተቀደሰ ፍልሚያ በተመለከተ መገናኚያ ብዙሓንን፦ ትዝብቱ ይሆን ሃዘኑ ወይስ ብስጭት ሃፍረቱ የበለጠ የጎዳኝ አላውቅም። ኹሉም ሳይደራረቡብኝ አልቀሩም፡

የጋዘጠኞች ዐላማ የተቀደሰና የተከበረ እንዲሁም የተደነቀ መሆኑን በአክብሮት ዐውቃለሁ። ይህን የተቀደሰ ዐላማ በታማኝነት ሠርታችሁበት/አልሠራችሁበት እንደሆን እያንዳንዳችሁ ከኅሊናችሁ ጋር ተነጋገሩበት፡፡ ለእምዬ ኢትዮጵያ ስትሉ ይህን ከኅሊና መወቃቀሳችሁን እንዳትሸሹት

**ዐደራ!        ዐደራ!!        ዐደራ!!!**

## ራድዮኖች ለአሜሪካና ለጀርመን ድምፆች ልኬ ነበር፤፡ ጭጭ ምንጭጭ

## ለጋዜጦች

አገር ውስጥ ለብዙዎቹ ተልኮ ጉግል ብቻ በማውጣቱ ለጉግል አክብሮቴና ምስጋናዬ ይድረስልኝ

## ድረ-ገጾች

ለዚህም ክፍል ባለቤቶች ለአብዛኛዎቹ ተልኮ አላወጡትም። አስቀድሜ ለአወጡት ለዕልቂት ባወጡት ስም እናንተንም ከግል ችግር ያውጣችሁ።

ሳታወጡ ለቀራችሁት ለሁላችሁም!

_ ከ 9 ሚሊዎን በላይ የሆኑ ወገኖቻችን ባለንበት ወቅት ርዳታ እንድሚያስፈልጋቸው አታውቁም?
_ ሉላዊው ሙቀት ድርቅንና ጎርፍን እንደሚያስከትል አታውቁም?
_ እነዚህ ቀውሶች የሚጠነክሩት አፍሪክ ላይ እንሆነ አታውቁም?
_ የአገራችን ወንዞች ለእነዚህ ቀውሶች ጠንቅም መድሃኒትም እንደሆኑ አታውቁም?

ታድያ የቀረቡትን ሽርክት መፍትሄዎች ሞልተው የተረፉ ባለሞያዎች ዐውቀው እንዳይምክሩበት ለጆሮቻቸውና ለዐይኖቻቸው ምቀኝነታችሁ ምንድን ነው? የወያኔን ዕድሜ ለማራዘም የሚሉ አንዳንዶች አሉ. ዕውን ይሄ የወያኔን ዕድሜ ያራዝማል?

## ያራዘመውስ የቅንጅትን ድል አሳልፎ የሠጠው!

## ለዚህ የእናንተስ ተጠያቂነት ምን ያህል ነው?

## ይልቅስ ከኅሊናም ከታሪክም ተወቃሽነት ለመዳን ማንንም ሳትፈሩ ለተቀደሰው ፍልሚያ ዐላማ በአንድ እንቁም!!